MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION
ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት
8221 Georgia Avenue, Silver Spring, MD. 20910
Tel: (202)-677-0094 Fax:
Web: http//www.moreshwegenie.org/

ቅፅ ፩ ፣ ቁጥር ፩ ፣ ታኅሣሥ ፲፪ ቀን ፪ሺህ፯ ዓ.ም.

# ሞረሽ የዜና መጽሔት

***ወቅታዊ በሆኑ ዐማራ-ነክ ጉዳዮች ላይ የምታተኩር የዜናዎች ጭማቂ የሚቀርብባትጋዜጣ***

አገራችን ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት ሁኔታ በጣም አስቸጋሪ ነው። በአሁኑ ሰዓት በድርቅ ምክንያት በተከሰተ ችጋር በርካታ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን በማለቅ ላይ ይገኛሉ። በተለይ የትግሬ-ወያኔ ዐማራውን ለይቶ ለማጥፋት ባለው ሥር የሠደደ ዓላማ ምክንያት በታች ጋይንት ፣ በስማዳ ቆላማ ቦታዎች ፣ በበለሳ ፣ በዋግ ፣ በደቡብ እና በሰሜን ወሎ፣ በምስራቅ ጎጃም የአባይ ሸለቆ ሕዝቡ የሚላስ የሚቀመስ ነገር የለውም።

ይህ አልበቃ ብሎ የትግሬ-ወያኔ አገዛዝ ሆን ብሎ አቅዶ በቆሰቆሰው የእርስ በእርስ ግጭት ምክንያት ለአያሌ ኢትዮጵያውያን መጨፍጨፍ፣ ለንብረቶቻቸውም መውደም ምክንያት ሆኗል። ለአብነት ያህል የአገዛዙ ሥርዓት «የአዲስ አበባ ከተማ የማስፋፊያ ማስተር ፕላን አዘጋጅቻለሁ፤ ያንንም አስፈጽማለሁ» በማለቱ አያሌ የኦሮሞ ተወላጆች ይህንን ውሣኔ ተቃውመው አመፅ አስነስተዋል። ከዚሁ የሕዝብ አመፅ ጋር በተያያዘ የአገዛዙ ሥርዓት ወታደሮች እና የፀጥታ ሠራተኞች ከ80(ሰማንያ) የማያንሱ ሰዎችን መግደላቸው በመገናኛ ብዙሃን ተገልጧል። ሆኖም ኦሮሞዎቹ በትግሬ-ወያኔ አገዛዝ ለሚደርስባቸው ጭፍጨፋ የብቀላ በትራቸውን የሚያሣርፉት ከእነርሱ በባሰ ሁኔታ በአገዛዙ እንዲጠፋ በተፈረደበት በዐማራው ላይ ሆኗል። «የኦሮሚያ ክልል» በሚባለው አካባቢ በሚገኙ በብዙ ከተሞች እና የገጠር ቀበሌዎች ፣ ኦሮሞዎች የዐማሮችን ቤት እና ንብረት እየለዩ በማውደም ላይ ናቸው፡፡ በአርሲ ብዙ ቤት ተቃጥሏል ፤ ከ5(አምሥት) በላይ ዐማሮች መገደላቸው ታውቋል። በምዕራብ ሸዋ አመያ ወረዳ ነዋሪ በነበሩ ዐማሮች ላይ ኦሮሞዎች በተቀነባበረ ሁኔታ በሰነዘሩት ጥቃት 1,000(አንድ ሺህ) ቤቶችን አቃጥለዋል። በማሣ እና በጎተራ ላይ የነበረውን የዐማራሮችን ሰብል እና ምርት ሙሉ በሙሉ አውድመውባቸዋል። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት «አህያውን ፈርቶ ዳውላውን» እንደሚባለው መሆኑን ማንም ጤነኛ እና አመዛዛኝ ኅሊና ያለው ሰው የሚፈርደው ነው።

## የጎንደር ዐማራ በሦሥት ጣምራ ጠላቶች ጥቃት ሥር ነው

በጎንደር ያለው ችግር ይበልጥ ተባብሷል። ሠሞኑን የትግሬ-ወያኔ በ«ቅማንት እና በዐማራ መካከል የተፈጠረ ግጭት» ብሎ በራሱ ካድሬዎች አማካይነት የጎንደርን ሕዝብ በጅምላ በመጨፍጨፍ ላይ ይገኛል። ከአካባቢው ከሚወጡ መረጃዎች እንደሚሰማው እስካሁን ከ800 የማያንስ ነዋሪ በተለያዩ መንገዶች ተጨፍጭፏል፦ አብዛኛው ግን በጥይት እየተደበደበ እንደተገደለ ይሰማል። በጭልጋ ፣ በመተማ እና በቋራ የበርካታ ሰዎች ቤቶች ተቃጥለዋል። ሌላው አስደንጋጭ ዜና ሆኖ የሰነበተው «የጎንደር ከተማ የመጠጥ ውኃ በመርዝ ተበክሏል» ወሬ ነበር። ሆኖም ስለዚህ ወሬ ትክክለኛነት እስካሁን የተገኘ ማረጋገጫ ባይገኝም፣ ከወያኔ መሠረታዊ ባሕርይ በመነሣት «አያደርጉትም» ብሎ መሞኘት አይቻልም።

የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት መምሪያ